# የክቡር መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ የሐንስ አጭር የሕይወት ታሪክ

1. **ልደት**፡ ክቡር መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ በምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት ፣ በባሶ ሊበን ወረዳ፣ ልዩ ስሙ ዶገም ኢየሱስ በተባለ ደብር ከአባታቸው ከአቶ ዮሐንስ ረአስና ከእናታቸው ከወ/ሮ እስቨቪያው ካሳ በ1935 ዓ/ም ተወለዱ፡፡

2. **ትምህርት፡**

ሀ. ዜማ

ክቡር መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ በተወለዱበት ደብር መርጌታ ተገኝ ረታ ከተባሉት የዜማ መምህር የንባብና የጽሕፈት ትምህርትን ከተማሩ በኋላ በዚሁ ደብር ጾዋትወ ዜማን ተምረው አጠናቀዋል፡፡

ለ. ቅኔ፡

ክቡር መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

- በምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት በመንግሥቶ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ከታዋቂው የቅኔ መምህር ከመምህር ደጉ ያሬድ
- በዚያው ሀገረ ስብከት ፣በእነብሴ ሣር ምድር በደብረ መድኃኒት ቅድስት ማርያም ደብር እስከ አሁን በሕይወት ካሉት ታዋቂ የቅኔ መምህር ከመምህር አስካል
- በሰሜን ጎንደር ሀገረ ስብከት፣ በተንከል ወረዳ፣ በደበጋ ቅዱስ ሚካኤል ደብር ከመምህር አክሊሉ ወርቅነህና ከሌሎችም መምህራን ቅኔ ከነአገባቡ፣ ዕርባ ቅምሩና ይትበሀሉ ተምረው በማጠናቀቅ በቅኔ መምህነት ተመርቀዋል፡፡

ሐ. ትርጓሜ መጻሕፍት፡

ክቡር መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ የተመረቁበትን የቅኔ ትምህርት እያስተማሩ በጎጃም ክፍለ ሀገር በዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም ከአለቃ ማርቆስ ብርሃኑ የፍትሐ ነገሥትና የዳዊት አንድምታ ትርጓሜን ተምረዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ወደ ጎንደር ተመልሰው በጎንደር መንበረ መንግሥት መድኃኔዓለም ከሊቀ ሊቃውንት መንክር መኮንን አቋቋም ተምረዋል፤ ከዚህም በኋላ በ1954 ዓ/ም ወደ አዲስ አበባ መጥተው በቀጨኔ ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በቅኔ መምህርነት ተቀጥረው እያስተማሩ ከመምህር ወንድማገኘሁ ወልደ ኪሮስ ሙሉ የሐዲሳት ትርጓሜን እንዲሁም በዚሁ ደብር ከነበሩት ከመምህር ጥበቡ......... የመጻሕፍተ ብሉያት ትርጓሜን ተምረዋል፡፡ በዚህም ወቅት ከልዩ ልዩ ሊቃውንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና የስብከት ዘዴን አጥንተዋል፡፡

በ1967 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ድርጅት አማካኝነት ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ኢንግላንድ ሂደው በፐሪስቶል/ pristole/ ትሪኒቲ ኮሌጅ የትምህርተ ኖሎት ጥናታቸውን አጠናቀው እ.አ. አ. በኅዳር 1978 ዓ/ም ዲፕሎማቸውን /Diploma in pastoral studies/ተቀብለዋል፡፡ በዚህ ወቅት የመጻሕፍተ ብሉያትንና ሐዲሳትን ትርጓሜ በጥልቀት ለመረዳት ወሳኝ የሆኑትን ፤የብሉይ ኪዳን ቋንቋ ዕብራይስጥንና የሐዲስ ኪዳን ቋንቋ ግሪክን ልዩ ትኩረት በመስጠት አጥንተዋል፡፡ የአማርኛ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላትን ከአዘጋጆቹ አንዱ በመሆን ያዘጋጁትም በዚህ ወቅት ነበር፡፡

በ1973 ዓ/ም የዓለም ክርስቲያናዊ የመገናኛ ዘዴዎች ማሰልጠኛ ድርጅት ባደረገላቸው ድጋፍ/ ስፖንሰርነት/ ስኮላርሽፕ አግኝተው ወደ ዛምቢያ ኪትዊ ሂደው በአፍሪካ የሥነ ጽሑፍ ማእከል ክርስቲያናዊ ሥነ ጽሑፍ፣ የጋዜጣና የመጽሔት አዘገጃጀት ትምህርቶችን ለ 6 ወራት ተከታትለው የምስክር ወረቀት አግኝተዋል፡፡

## 3. ሥራና አገልግሎት፡

ክቡር መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ከ1954 እስከ 1959 ዓም በቀጨኔ ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን የቅኔ መምህር ሆነው አስተምረዋል፡፡ ከ1959 እስከ 1961 ዓ.ም. ድረስ በታላቁ የመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ለሕትመት የሚቀርቡ መጻሕፍትን በመተርጎም፣ የተተረጎሙትን በቁም ጽሕፈት በማዘጋጀት፣ ለሕትመት የተዘጋጁትን በማረምና የሕትመት ሥራውን በመከታተል ሲሠሩ ቆይተዋል።

በ1961 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ድርጅት በመዛወር በብሥራተ ወንጌል ሬዲዮ ጣቢያ ትምህርተ ወንጌል በመስጠት፣ ግእዝ በሬዲዮ በሚል ርእስ የግእዝ ቋንቋ ትምህርትን በማዘጋጀትና በማቅረብ፣ በተለያዩ ገዳማትና አድባራት ተዘዋውረው ለካህናት ስልጠናን ለምእመናን ትምህርተ ወንጌልን በማዳረስ፣ የትንሣኤ መጽሔት ዋና አዘጋጅ በመሆን ከሚያቀርቧቸው ጽሑፎች በተጨማሪ በድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣ ያለማቋረጥ በተለያዩ የትምህርት አርእስት በጥናት ላይ የተመሠረቱ ጽሑፎችን በማቅረብ ሰፊ አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡

በ1963 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ድርጅት ባቋቋመው የሥነ ምግባር ጓድ ውስጥ ኀላፊ በመሆን ለሥነ ምግባር ትምህርት መዳበር ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡

ክቡር መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ መስከረም 7 ቀን 1974 ዓ.ም. ቅዱስ ሲኖዶስ ባሳለፈው ውሳኔ መሠረት፣ ከጥር 6 ቀን 1974 ዓ.ም. ጀምሮ በዚያን ጊዜ ሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት በአሁኑ ሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ የብሉይ ኪዳን መምህር ሆነው እንዲያስተምሩ ተመደበው በማስተማር ላይ እንዳሉ የካቲት 2 ቀን 1974 ዓ.ም. ደግሞ ከብሉይ ኪዳን መምህርነታቸው በተጨማሪ የትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር፣ የቦርድ አባል፣ የሥርዐተ ትምህርት አዘጋጅ ኮሚቴ አባል፣ የጥናትና የተማሪዎች ዲን / dean of studies and students/ በመሆን ለቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል:: የካቲት 14 ቀን 1977 ዓም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ለሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት የብሉይ ኪዳን ቋሚ ማስተማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅተው ማቅረባቸውን በማድነቅ መጋቤ ብሉይ የሚለውን የመዐርግ ስም ሰጥተዋቸዋል:: ያዘጋጁት የብሉይ ኪዳን ማስተማሪያ መጽሐፍም እስከ አሁን ድረስ የኮሌጁ የብሉይ ኪዳን ማስተማሪያ በመሆን ያገለግላል::ክቡር መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ልዩ የማስተማር ጸጋ፣ የማመስጠርና የማስረዳት ችሎታ የነበራቸው ታላቅ መምህር እንደነበሩም ደቀ መዛሙርቶቻቸው ይመሰክሩላቸዋል::

ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዝደንት፣ የዓለም ሃይማኖቶች ለሰላም የክብር ፕሬዝደንት ከፍተኛ ጥረት እንደገና ተከፍቶ ማስተማር ሲጀምር ከመደበኛ ሥራቸው በተጨማሪ የሥርዐተ ትምህርት አዘጋጅ ኮሚቴ አባል፣ የብሉይ ኪዳን መምህር በመሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል::

ክቡር መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ከጥቅምት 1 ቀን 1988 ዓ.ም. ጀምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ አባል፣ ከግንቦት ወር 2001 ዓም ጀምሮ የሊቃንት ጉባኤ መምሪያ ኀላፊ በመሆን በሥጋ እስከ ዐረፉበት ዕለት ድረስ ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳይሉ በታላቅ ትጋት ቤተ ክርስቲያኝን አገልግለዋል::

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከግእዝ ዘርና ከሰብአ ሊቃናት ትርጉም ጋር ተገናዝቦ በ2000 ዓ.ም. በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር አሳታሚነት በታተመው የመጽሐፍ ቅዱስ ሥራ ከ1986 ዓም ጀምሮ የዝግጅት ኮሚቴው አባልና ምክትል ሰብሳቢ ሆነው መጽሐፉ እስከ ታተመበት ጊዜ ድረስ በግንባር ቀደም አዘጋጅነት ለሕትመት እንዲበቃ ከዳረጉት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ተቀዳሚው ነበሩ:: እስከ አሁንም ድረስ

ከአንባብያን የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በመቀበል ለድጋሚ ሕትመት በሚደረገው ሥራ ላይ እጅግ በተፋጠነ ሁኔታና በከፍተኛ ትጋት በመሥራት ላይ ነበሩ፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፣ ሥርዐተ አምልኮና የውጭ ግንኙነት የሚለው መጽሐፍ በተዘጋጀ ጊዜም የአዘጋጅ ኮሚቴው አባል በመሆን የላቀ አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡

## 4. ልዩ ልዩ የሥራ ተሳትፎና ተልእኮ

በ29/6/1991 ዓም ወደ ኢጣሊያ ቫቲካን ተልከው በቫቲካን የሚገኙ ጥንታውያን የኢትዮጵያ መጻሕፍትን በተመለከተ ጥናት አጥንተው ተመልሰዋል፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት አካዳሚ ካሳተማቸው የግእዝ ቅኔያትና የሥነ ጥበብ ቅርስ በሚል ርእስ ከተዘጋጁት አራት የቅኔ መጻሕፍት መካከል ክፍል ሦስትንና አራትን በመተርጎም፣ በማመስጠርና በመተረክ አዘጋጅተዋል፡፡ በዩኒቨርስቲው የኢትዮጵያ ባሕልና የቋንቋዎች ጥናት አካዳሚ የቦርዱ የጠቅላላ ጉባኤ አባል፣ የሥራ አስፈጻሚው አባል፣ እንዲሁም የግእዝ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ ኮሚቴ ተጠሪ በመሆን ተመርጠው በማገልገል ላይ ነበሩ፡፡ በየጊዜው ከመንፈሳዊ ኮሌጅና ከአዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ የሚመረቁ ተማሪዎች የመመረቂያ ጽሑፋቸውን በሚያዘጋጁበት ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የተመለከቱ መረጃዎችን በመስጠትና በማማከር ደከመኝ፤ ሰለቸኝ ሳይሉ ምሁራዊ ግዴታቸውን ተወጥተዋል፡፡

እንዲሁም በ2002 ዓ.ም. የታተሙትን የታላቁን ሊቅ የመምህር አካለወልድን ቅኔዎች ተርጉመዋል አመስጥረዋል፡፡ የታላቁን ሊቅ የመልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬን <u>ዝክረ ሊቃውንት</u> የተሰኘውን ክፍል ሁለት የቅኔ መጽሐፍም የአርትኦት ሥራ ሠርተዋል፡፡

ከ1997 ዓ.ም. ጀምሮ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር የዕድሜ ልክ አባል፣ የቦርድ አባልና የትርጉም ኮሚቴ አባል በመሆን እስከ ዕለተ ዕረፍታቸው በነበራቸው ከፍተኛ እውቀት ማኅበሩን በቅንነት አገልግለዋል፡፡

ቤተ ክርስቲያናችን የሚሊኒየምን በዓል በምታከብርበት ወቅት የበዓሉ አዘጋጅ ዐቢይ ኮሚቴና የሥነ ጽሑፍ ኮሚቴ አባል በመሆን ያገለገሉ ከመሆናቸውም በላይ የጥንታውያን ገዳማትን ታሪክ በተመለከተ በሲዲ የተዘጋጀውን ትረካ አቅርበዋል፡፡

እንዲሁም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከልደተ ክርስቶስ እስከ 2000 ዓ.ም. በሚል ርእስ የተዘጋጀችውን መድበለ መጻሕፍት ካዘጋጁት ሊቃውንት አንዱ በመሆን የአንድምታ ትርጓሜን በተመለከተ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርበዋል፡፡

የልማት ወንጌል በሚል ርእስ ከመጽሐፈ ግጻዌ ጋር በተገናዘበ መልኩ ተዘጋጅቶ የታተመውን የ365 ቀናት የስብከት ማስተማሪያ መጽሐፍ ከሌሎች ሊቃውንት ጋር አዘጋጅተውና አርመው እንዲታተም አድርገዋል፡፡ከዚሁ ጋር በተያያዘም ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በተመለከተ አድልዎና መገለል እንዳይኖር የሚያስተምር መጽሐፍ ከሊቃውንት ወንድሞቻቸው ጋር አዘጋጅተው ለኅብረተ ሰብ እንዲዳረስ አድርገዋል፡፡

ክቡር መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ባላቸው ጥልቅ የቤተ ክርስቲያን እውቀትና በቀሰሙአቸው የተለያዩ ሙያዎች በዚህ አጭር ጽሑፍ ተዘርዝረው የማያልቁ በጥናት ላይ የተመሠረቱ ጽሑፎችን በጋዜጦችና በመጽሔቶች ጽፈዋል፤ በተለያዩ አውደ ጥናቶችም በርካታ ጥናታዊ ጽሑፎችን በማቅርብ የሚጠበቅባቸውን ሙያዊ ድርሻ በተገቢ ሁኔታ ፈጽመዋል፡፡የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምታከብራቸውን ታላላቅ ብሔራውያን በዓላት በተመለከተ በየጊዜው በመጽሔቶችና በጋዜጦች ላይ መንፈሳውያት ጽሑፋትን አቅርበዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በመወከል እየተላኩ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት አጠቃላይ ጉባኤና በተለያዩ ሀገሮች በተደረጉ ልዩ ልዩ ጉባኤያት በመገኘት የቤተ ክርስቲያኒቱን መልእክት በተገቢው ሁኔታ በማድረስ የቤተ ክርስቲያንን ዓለም አቀፋዊ ተልእኮ ፈጽመዋል፡፡

ክቡር መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ በተለይም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ፓትርያርኮች እንደ ዘመን መለወጫ፣ ልደትና ፋሲካን በመሳሰሉት ዐበይት በዓላት የሚያስተላልፏቸውን ምእዳናት ከቅዱሳን ፓትርያርኮች መመሪያ እየተቀበሉ በማዘጋጀትና በማቅረብ ቅድስናና በረከትን የተመላ አገልግሎት ሲፈጽሙ ኑረዋል፡፡

## 5. የስብከተ ወንጌል አገልግሎት

ክቡር መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ከላይ በአጭሩ እንደ ተገለጠው በልዩ ልዩ የመገናኛ ዘዴዎችና በአካል እየተገኙ የትምህርተ ወንጌል አገልግሎት ያልሰጡበት ቦታ አለ ለማለት ያስቸግራል፡፡ ሆኖም በተለይ እስከ አሁን ድረስ የትምህርተ ወንጌል አገልግሎታቸውን በቋሚነት ከሰጡባቸው ገዳማትና አድባራት፡-

- የደብረ ጽጌ ቅዱስ ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን
- የመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል
- የቀጨኔ ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን
- የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም
- የጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ከዚህም ጋር ክቡር መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ በየወሩ በ19 በቅዱስ ገብርኤል ስም ለሚሰበሰቡ የማኅበር አባላት፣ በ27 በመድኃኔዓለም ስም ለሚሰበሰቡ ምእመናን ቋሚ ትምህርተ ወንጌል ይሰጡ ነበር፡፡ ክቡር መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ዓለም አቀፍ በሆነው ጥልቅ እውቀታቸው፣ በትምህርተ ወንጌል አቀራረባቸው፣ በጣዕመ ስብከታቸውና በጊዜ አጠቃቀም ችሎታቸው በማኅበረ ካህናትና በማኅበረ ምእመናን እጅግ በጣም ተወዳጅና ተናፋቂ ሐዋርያ ነበሩ፡፡

## 6. የካህናት ስልጠና

ከላይ እንደተገለጠው በመደበኛ መምህርነትና ርእሰ መምህርነት ያሰለጥኑባቸው ከነበሩት ከቅዱስ ጳውሎስና ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጆች በተጨማሪ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በተቋቋሙት የካህናት ማሰልጠኛዎች ማለትም

- በአዲስ አበባ
- በባሕር ዳር
- በመቀሌ
- በጋሞጎፋ ሀገረ ስብከት በጨንቻ አውራጃ
- በኢሉባቦር ሀገረ ስብከት በመቱ በነበሩት የካህናት ማሰልጠኛዎች እየተላኩ ስልጠና በመስጠትና ለማሰልጠኛዎች የማስተማሪያ መጻሕፍትን በማዘጋጀት ከፍተኛ አገልግሎት አበርክተዋል፡፡ በዚህም አገልግሎታቸው ክቡር መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ በአሁኑ ጊዜ ያሉትን ሰባክያነ ወንጌልና ካህና ት በትምህርት የ ወለዱ የእ ውቀት ምንጭ ነበሩ፡፡

## 7. የቤተሰብ ሕይወት

ክቡር መጋቤ ብ ሉ ይ ሰይ ፈ ሥ ላሴ ዮሐንስ ሐምሌ 15 /1961 ዓ.ም. ከባለቤታቸው ከወ/ሮ ፈለቀች ተመስገን ጋር በቤተ ክርስቲያን ሕግ መሠረት በሥርዐተ ተክሊል ተጋብተው ሦስት ወንዶች ልጆችን አፍርተዋል፡፡

## 8. የክቡር መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ልዩ የመገለጫ ባሕርያት

ክቡር መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ባሕረ ትዕግሥታቸው ተጠልቆ የማያልቅ ታጋሽና ትሑት፣ ለተጠየቁት ጥያቄ በቂ፣ በምክንያትና ማስረጃ ላይ የተመሠረተ ፈጣን መልስ መስጠት የሚችሉ፣ ቅን ታዛዥ፣ ትጉህ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን መመርመርና ማመስጠር ልዩ መገለጫዎቻቸው የሆኑ፣ ለበጎ ነገር ከሆነ ለበላይ አካል ብቻ ሳይሆን ለማንኛውም ሰው እንቢታን የማያውቁ፣ በእውቀታቸው ጥቅምን የማይጠይቁ ታላቅ ሊቅ ነበሩ፡፡

ይሁን እንጂ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወእፈቱሰ እፍልስ ወእትፈለጥ እም ዝንቱ ዓለም ወእህሉ ኀበ ክርስቶስ፤ ወፈድፋደሰ ይኄይስ ወይደሉ ሊተ ዝንቱ፡ ትርጉም እኔስ ከዚህ ዓለም ተለይቼ ልሄድና በክርስቶስ ዘንድ ልኖር እወዳለሁ፤ ይልቁንም ለእኔ ይህ ይሻለኛል፤ ይበልጥብኛልምና ፊል. 1፤23፡፡ ሠናየ ገድለ ተጋደልኩ፤ በድርየኒ ፈጸምኩ፤ ወሃይማኖትየኒ ዐቀብኩ፡፡ እንከሰ ጽኑሕ ሊተ አክሊለ ጽድቅ ዘየዐስየኒ እግዚአብሔር መኰንነ ጽድቅ ይእተ ዕለተ ትርጉም መልካም ገድልን ተጋደልሁ፤ ሩጫየንም ፈጸምሁ፤ ሃይማኖቴን ጠበቅሁ፤ እንግዲህስ በዚያች ቀን እውነትን የሚፈርድ እግዚአብሔር የሚሰጠኝ የጽድቅ አክሊል ይጠብቀኛል 2 ጢሞ 4፡7-8 እንዳለው ክቡር መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ለቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ አገልግሎት በመፋጠን ላይ እንዳሉ ለከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ወደ አሜሪካ ተልከው ተልእኳቸውን ፈጽመው ነሐሴ አንድ ቀን 2002 ዓም ከጥዋቱ ሦስት ሰዓት ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ሲደርሱ ከአውሮፕላን እንደ ወረዱ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ሕመም ወዲያውኑ ወደ ሆስፒታል ተወስደው በምርመራ ላይ እንዳሉ በተወለዱ በ 67 አመታቸው ዐርፈዋል፡፡

እሑድ ነሐሴ 2 ቀን ከቀኑ 10 ሰዓት ጀምሮ አስከሬኑ ከነበረበት ሆስፒታል መኖሪያቸው ወደ ሆነውና ሲያገለግሉበት ወደ ነበረው የቀጨኔ ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ተወስዶ ጸሎተ ፍትሐትና ሙሉ አደራረስ ሲደረግ አድሯል፣ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዝደንትና የዓለም ሃይማኖቶች ለሰላም የክብር ፕሬዝደንት መመሪያ ሰጭነት በሊሎች የአዲስ አበባ ገዳማትና አድባራትም ጸሎተ ፍትሐት ተደርጓል፡፡ ሰኞ ነሐሴ 3 ቀን ከጥዋቱ 3 ሰዓት ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ፣ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ የመ/ፓ/ጠ/ቤ/ክ/ የየመምሪያ ኀላፊዎችና ሠራተኞች፣ የገዳማት አበምኔቶችና የአድባራት አስተዳዳሪዎች፣ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች፣ ወዳጅ ዘመድና በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ምእመናን በተገኙበት ወደ መንበረ ጸባኦት

ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተወስዶ ጸሎተ ፍትሐት ሲደረግ ውሎ በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ መሪነት ሥርዐተ ቅዳሴ ከተፈጸመ በኋላ ከቀኑ 9 ሰዓት ላይ ሥርዐተ ቀብራቸው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዝደንትና የዓለም ሃይማኖቶች ለሰላም የክብር ፕሬዝደንት፣ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት፣ የመ/ፓ/ጠ/ቤ/ክ/ የየመምሪያ ኀላፊዎችና ሠራተኞች፣ የገዳማት አበምኔቶችና የአድባራት አስተዳዳሪዎች፣ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች፣ወዳጅ ዘመድና በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ምእመናን በተገኙበት ተፈጽሟል።

በክቡር መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ዕረፍት መሪር ሐዘን የደረሰባቸው ቤተ ሰቦቻቸውና ወዳጅ ዘመዶቻቸው ብቻ ሳይሆኑ በቅንነትና በታማኝነት ያገለገሏት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባታል።

ስለዚህ ለክብርት ባለቤታቸው፣ ለልጆቻቸውና ለቤተ ሰቦቻቸው መጽናናትን እንዲሰጥ፣ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም እንደ እርሳቸው ያለ ቅንና ታዛዥ ምሁር እንዲተካላትና ለነፍሳቸው ዕረፍተ መንግሥተ ሰማያትን እንዲሰጥ ቤተ ክርስቲያን ወደ እግዚአብሔር ትጸልያለች።

ነሐሴ 3 ቀን 2002 ዓ.ም.

አዲስ አበባ